## እውነታ ጽሁፍ ወረቀት

# በዘር ጎሳ አድልዎ ፈጠራ አንቀጽ ህግ መሰረት ቅሬታዎች

## የዘር ጎሳ አድልዎ ፈጠራ አንቀጽ ህግ ምንድ ነው?

*የዘር ጎሳ አድልዎ ፈጠራ አንቀጽ ህግ/Racial Discrimination Act 1975* (Cth) (the RDA) እንዳወጣው በርስዎ ዘር ጎሳ፤ የቆዳ ቀለም፤ የመጡበት አገር ወይም ጎሳ ወይም የስደተኛ ሁኔታ ተመርኩዞ ያላግባብ እርስዎን ማስተናገድ ህገ-ወጥነት ነው።

እንዲሁም የዘር ጎሳ ጥላቻ ህገ-ወጥነት ነው።

## መቸ ነው ይህንን መጠቀም የሚቻል?

ለRDA አንቀጽ ህግ መጠቀም የሚችሉት በአብዛኛው ህዝባዊ ህይወት መገልገያ ቦታዎች ላይ በአግባቡ መስተንግዶ ለማግኘት ነው:

- ***ሥራና ሰራተኛ* –** *ሥራ ለማግኘት፤ ለሥራ ሁኔታና ቅድመ ሁኔታዎች፤* ስልጠና፤ እድገት፤ ከሥራ መባረር።
- **ትምህርት –** በግል ወይም በመንግሥት ትምህርት ቤቶች፤ በኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ለመመዝገብ ወይም ለመማር።
- **መጠለያ ቦታ –** ቤት ወይም ዩኒት ስለመከራየት ወይም ስለመግዛት።
- **አገልግሎቶችን ማግኘት ወይም መጠቀም –** እንደ ባንክ ወይም ኢንሹራንስ፤ በመንግሥት መምሪያዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች፤ ትራንስፖርት ወይም ተለኩሚኒኬሽን አገልግሎቶች፤ የሙያ አገልግሎቶች እንደ በህግ ጠበቃ፣ ሀኪሞች ወይም በንግድ ሰዎች የሚቀርቡ ማለት በሬስቶራንቶች፤ ሱቆች፤ ወይም በመዝናኛ ቦታውች ለሚቀርቡ አገልግሎቶች ይሆናል።
- **ህዝባዊ ቦታዎችን ስለመጠቀም –** እንደ መናፈሻ ቦታዎች፤ የመንግሥት ቢሮዎች፤ ሬስቶራንቶች፤ ሆተሎች ወይም የመገበያያ ማእከላት ያሉትን።

## የዘር ጎሳ አድልዎ ፈጠራ ምንድ ነው?

የዘር ጎሳ አድልዎ የሚፈጠረው በተመሳሳይ ሁኔታ ባለ ሰው ላይ ባለው የዘር ጎሳ፤ ቆዳ ቀለም፤ ትውልድ አመጣት፤ የመጣበት አገር ወይም ጎሳ ወይም የስደት ሁኔታን ምክንያት በማድረግ አንድ ሰው ያላግባብ ዝቅ አድርጎ ሲያስተናግድ ነው። ለምሳሌ፡ ተከራዩ ለየት ካለ ጎሳ ስለመጣ ወይም በቆዳ ቀለም ሳቢያ የንብረት አከራይ ተወካይ ቤቱን አላከራይም ካለ ይህ 'ቀጥታ አድልዎ ፈጠራ' ሊሆን ይችላል።

እንዲሁ የጎሳ አድልዎ የሚፈጠረው ለሁሉም አንድ ዓይነት የሆነ ደንብ ወይም ፖሊሲ ባለበት ላይ ነገር ግን ሰዎችን ባላቸው የዘር ጎሳ፤ ቆዳ ቀለም፤ ትውልድ አመጣት፤ የመጣበት አገር ወይም ጎሳ ወይም የስደት ሁኔታን ሳቢያ ሰዎች ያላግባብ የመስተናገድ ችግር ይደርስባቸዋል። ይህም 'በተዘዋዋሪ አድልዎ ፈጠራ' ይባላል። ለምሳሌ፡ ኩባንያው በሥራ ቦታ ተቀጣሪዎች ባርኔጣ ወይም ሌላ የጭንቅላት መሸፈኛ ማድረግ የለባቸውም ካለ ይህ በተዘዋዋሪ አድልዎ ፈጠራ ሊሆን ሲሆን ይህም ከሌላ ጎሳ/ዘር ለመጡ ሰዎች ያላግባብ የሆነ ችግር ይፈጥርባቸዋል።

## የዘር ጎሳ ጥላቻ ምንድ ነው?

በአንድ ሰው ወይም በስብስብ ሰዎች ላይ ከዘር ጎሳ፤ ቆዳ ቀለም፤ ትውልድ አመጣት፤ ከመጣበት አገር ወይም ጎሳ ጋር በተዛመደ ሰዎችን **ሊያበሳጭ፤ መሰደብ፤ ማዋረድ ወይም ሊያስፈራራ** ስለሚችል በህዝባዊ ስፍራ ማካሄድ ህገ-ወጥነት ነው።

በጎሳ ጥላቻ ምሳሌዎች ሊካተት የሚችል ጎሳን መሰረት አድርጎ:

- በኢንተርኔት ላይ የጥቃት መልእክት ማስተላለፍ፤ ይህም በኢፎሩምስ/e-forums፣ ብሎግስ፣ ማሕበራዊ መገናኛ ቦታዎች እና በቪዲዮ ተሳትፎ ቦታዎችን ያካተተ
- የጥቃት አስተያየቶችን ወይም እይታዎችን፣ በህትመት ወረቀት እንደ ጋዜጣ፤ መጋዜኖች ጽሁፍ ወረቀት ወይም በራሪ ወረቀት
- ህዝብ በተሰበሰበበት ላይ የጥቃት ንግግሮች
- በህዝባዊ ቦታዎች ላይ እንደ ሱቅ፤ የሥራ ቦታ፤ መናፈሻ ቦታ፤ በህዝባዊ መጓጓዣ ወይም በትምህርት ቤቶች ላይ የስድብ ወረርሽኝ አስተያየቶች
- በስፖርት ድርጊቶች ላይ በተጨዋቶች፤ በተመልካቾች፤ አሰልጣኞች ወይም በሀላፊዎች የስድብ አስተያየቶች

## በህገ-ወጥነት መሰረት ሳይሆን በአጥቂነት ባህሪ የሚሆነው መቼ ነው?

የ RDA አንቀጽ ህግ ዓላማ በነጻነት የመነጋገር መብትን ለማስተካከል ('የንግግር ነጻነት') እና ከጎሳ ጥላቻ ነጻ በሆነ ለመኖር መብትን ማስጠበቅ ይሆናል። የ RDA አንቀጽ ህግ እንደሚለ የሚከተሉት ነገሮች ህገወጥ እንዳልሆኑ ታዲያ እነዚህ ነገሮች **"ምክንያታዊና በጥሩ እምነት ከተፈጸመ"** ይህም:

- **በስነጥበባዊ ሥራ ወይም ድርጊት ፍጻሜ** – ለምሳሌ፡ በጨዋትው ላይ የጎሳ ጥቃት ባህሪ የሚታይ ከሆነ ነው።
- **የጽሁፍ መግለጫ፣ ህትመት፣ ንግግር ወይም ሃቅነት ያለውን የአካዳሚክ ወይም ሳይንሳዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት ለመፍጠር** – ለምሳሌ። በህዝባዊ ፖሊሲዎች እንደ ኢሚግሬሽን፤ መድብለባህላዊ ወይም ለየት ባሉ እርምጃዎች ላይ ለየት ካሉ ቡድኖች ጋር ውይይት ማካሄድ።
- **ስለህዝባዊ ፍላጎት በተመለከተ ጉዳይ ላይ አግባብ ያለውና ትክክለኛ ሪፖርት ማቅረብ** – ለምሳሌ፡ ስለ የዘር ጎሳ ጥቃት ተግባር በጋዜጣ ውስጥ አግባብ ያለው ሪፖርት ማቅረብ።
- **አግባብ ያለው አስተያየት መስጠት፤** የተሰጠው አስተያየት ስለ ሰውየው ትክክለኛ እምነት የሚገልጽ ከሆነ ነው።

## በጎሳ ጥላቻ ወይም አድልዎ ፈጠራ ከደረሰብኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ይህን በቀጥታ ካደረሰው ወይም ከተሳተፈ ሰው ጋር ማንሳት ይችላሉ።

በዚህ መፍትሄ ካላገኙ፤ ወይም ይህን ለማካሄድ ምቹነት ስሜት ከሌለዎት ታዲያ ለአውስትራሊያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ያለዎትን ቅሬታ ማመልከት ይችላሉ። እንዲሁም የሆነ ሰው እንደ ጠበቃ፤ አማካሪ ወይም እርስዎን ወክሎ የሚያነጋግር የቅሬታ ንግድ ማሕበር ተወካይ ማቀናጀት ይችላሉ።

ለኮሚሽኑ ቅሬታን ለማስገባት ምንም ዓይነት ክፍያ ወጪ ለውም።

የርስዎ ቅሬታ በጽሁፍ መሆን አለበት። በኮሚሽኑ ለቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ስላለው ታዲያ መሙላት እንደሚችሉና በፖስታ ወይም በፋክስ አድርገው ወደ እኛ መላክ ወይም ያለዎትን ቅሬታ በኦንላይን በእኛ ድረገጽ ላይ ማስገባት ይችላሉ። ቅሬታዎን በጽሁፍ ማስቀመጥ ካልቻሉ ልንረዳዎ እንችላለን።

የርስዎ ቅሬታ ዋጋ እንዲያገኝ ማቅረብ ለፈለጉት ቅሬታ ስለ ህገወጥነት አድልዎ ፈጠራ ድርጊት ምክንያታዊ የሆነ አከራካሪ መሆን እንዳለበትና ስለሚያቀርቡት ክስ በቂ ዝርዝር መረጃ፤ ይህም ምን እንደተፈጠረ፤ መቼና የት እንደሆነ እንዲሁም ማን ተሳትፎ እንደነበር መረጃ ማቅረብ አለብዎት።

ቅሬታው በማንኛውም ቋንቋ ሊቀናጅ ይችላል። ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ካስፈለግዎት ልናቀናጅልዎት እንችላለን።

## በበለጠ መረጃ የት ማግኘት እችላለሁ?

ለአውስትራሊያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ለማነጋገር ዝርዝር መረጃዎች:

**ተለፎን**
የአገር አቀፍ መረጃ አገልግሎት በስልክ: 1300 656 419 ወይም (02) 9284 9888
መስማት ለተሳነው/TTY: 1800 620 241 (በነጻ ጥሪ)
ፋክስ: (02) 9284 9611

**በፖስታ**

GPO Box 5218
Sydney NSW 2001

**በኦንላይን መስመር**
ኢሜል: infoservice@humanrights.gov.au
ድረገጽ: www.humanrights.gov.au

በመስመር ላይ ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉት በድረገጽ
www.humanrights.gov.au/complaints_information/online_form/index.html.

ደንቆሮ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት ለTTY በስልክ 1800 620 241 አድርጎ እኛን ማነጋገር ይችላሉ። በምልክት/Auslan አስተርጓሚ ካስፈለግዎት ልናቀናጅልዎ እንችላለን።

አይነ ስውር ወይም የማየት ችግር ካለብዎት መረጃን በሌላ ቅርጽ ሲጠይቁ ማቅረብ እንችላለን።

### ለዘር ጎሳ ጥላቻ ቅሬታዎች ሌላ መገናኛ ቦታዎች

ስለ አጥቂ መገናኛ ብዙሃን ታሪክ፤ የዜና ማሰራጫ ወይም የኦንላይን መስመር ይዘት በተመለከተ አሳሳቢ ጉዳይ ካለዎት ለአውስትራሊያ መገናኛና መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን (ACMA) ቅሬታ ማስገባት ሲችሉ; ለማስታወቂያ ከሆነ ለማስታወቂያ ደረጃ ቦርድ; ወይም ለጋዜጣ ታሪኮች ከሆነ ለአውስትራሊያ ህትመት ምክር ቤት ቅሬታ ማስገባት ይችላሉ። እንዲሁም ለብዙሃን መገናኛ ኢዲቶር ወይም አስተዳዳሪ ድርጅት ቅሬታን ማስገባት ይችላሉ።

በጎረቤታሞች ስለሚፈጠር አጥቂነት ባህሪ የሚያሳስብዎት ከሆነ ችግሩን ለመፍታት ለማህበረሰብ ፍትሕ ማእከል ማነጋገር ሲችሉ፤ ወይም በመንግሥት መኖሪያ ቤት የሚኖሩ ከሆነ ለመኖሪያ ቤት መምሪያ ማነጋገር።

**ከተስፈራሩ፤ በሁከት ወይም ጠበ ጫርነት ከተጠቁ ጥቃት ከደረሰብዎ ወደ ፖሊስ መሄድ ነው።**

*አጠቃላይ ህጋዊ የሆነ ምክር*

ቅሬታ ለማቅረብ እያሰቡ ከሆነ፤ ህጋዊ የሆኑ ምክር ማግኘት ወይም ለርስዎ ንግድ ማሕበር ማነጋገር ሊያስፈልግዎት ይችላል። ስለ አድልዎ ፈጠራና ማስፈራራት በተመለከተ ህጋዊ የሆነ ምክር ያለክፍያ በነጻ ማቅረብ የሚችሉ የማህበረሰብ ህጋዊ ምክር አገልግሎቶች እንዳሉ ነው። በአቅራቢያዎ ለሚገኝ የማህበረሰብ ህጋዊ ምክር አገልግሎት በድረገጽ፡ (www.naclc.org.au/directory) ላይ ማግኘት ይቻላል።

**የክህደት ቃል: በዚህ እውነታ ጽሁፍ ላይ ያለው መረጃ እንደ መመሪያ ብቻ ተብሎ የታሰበ ነው። ለህጋዊ የሆነ ምክርን እንደማተካ ነው።**